# ሃጎስ ብሎ አማራ ፣ ድጋሚ ኪሳራ

ወይራ ዶግ ወለደ ፣ ዘመን ተቀየረ
ቅል የበላይ ሆኖ ፣ ድንጋይ ተሰበረ
ባንዳ አንገቱ ቀና ፣ ጀግና አቀረቀረ
ባለጌ ተከብሮ ፣ ጨዋ ሰው አፈረ
ደንቆሮ እየመራ ፣ ያካል የተማረ
እሬቱ ጣፈጠ ፣ ማሩ እየመረረ
ቀድሞ የምናውቀው ፣ ወዴት ተሰወረ ።

በጣም ያሳዝናል ፣ የማይሆነው ሲሆን
ለሌሎች የምንተርፍ ፣ ለራሳችን ሳንሆን
በአረር እየቆሉ ፣ ሲማግዱን እቶን
ስለመብት መቆም ፣ መናገር አቅቶን
አጎብዳጆች ስንሆን ፣ ፍርሃት አምቆን
ያበሉን ያጠጡን ፣ ያለበሱን ሞቆን
የጣሉልን ዲናር ፣ ይሆናል ተናንቆን
አሊያም ፈጣሪ ፣ አምላካችን እርቆን ።

በእለተ አድዋ ፣ በጀግኖች ቀናቸው
ኢትዮጵያን ባቆሙ ፣ በምንኮራባቸው
ፓርላማ ታጉረው ፣ አማራ ያልናቸው
በናት ይሆን ባባት ፣ ባጥንት በዘራቸው
እንዲህ ያለ ውርደት ፣ ያልተሰማባቸው
አማራውን እረድ ፣ ብለው መምረጣቸው
በራሳቸው መፍረድ ፣ ይሆን ከልባቸው
ወይስ ሁሉም ሃጎስ ፣ በረከቶች ናቸው ።

የጎጠኞች ስርዓት ፣ ጥላቻ የሚዘራ
እንዳሻው መንዛሪ ፣ ለነሱ እስከሰራ
በረከት ህላዊ ፣ የሚባል አማራ
ምድቡ የነበር ፣ ከነትክላይ ጋራ
ፓርላማ ሰግስገው ፣ ባመቻቹት ሴራ
ዛሬ ባማራው ስም ፣ አይሰሩ ተሰራ
ሃጎስ ብሎ አማራ ፣ ድጋሚ ኪሳራ
አዋጅ አፀደቀ ፣ ለሞቱ ሳይራራ ።

ታዛቢው

March 3, 2018